# ስራ

ወደ ሥራ ገበያ መግቢያ
ስራ ማግኘት
መብት እና ግዴታ
ስራ አጥነት
የዲፕሎማ ዕውቅና

# ወደ ሥራ ገበያ መግቢያ

**አንድ ሰው በስዊዘርላንድ ውስጥ ስራ ተቀጥሮ እንዲሠራ ወይም ድርጅት ማቋቋም እንዲችል፣ ዜግነቱ እና ወደ ስዊዘርላንድ የመጣበት ምክንያት ይወሰናል። በማንኛውም ሁኔታ ሰራተኞች በማህበራዊ መድን ዋስትና የግድ መመዝገብ እና ታክስ መክፈል አለባቸው።.**

## የስራ ፈቃድ

አብዛኛውን ግዜ የመኖሪያ ፈቃድ ከተሰጠ የስራ ፈቃድ በአንድ ላይ ነው የሚሰጠው፣ ስለዚህ የስራ ፈቃድ ጥያቄ በዚሁ መልስ ያገኛል። በመሰረቱ የመኖር መብት ያላቸው ሰዎች ስዊዘርላንድ ውስጥ ስራ መስራት ይፈቀድላቸዋል። እንደ ዜግነቱ እና የስራው ርዝማኔው ታይቶ ስራ ቀጣሪው ወይም ሰራተኛው የስራ ፈቃድ ያመለክታል። እርግጠኛ ለመሆንና ለማጣራት ከዚህ በታች የተጠቀሱት ቢሮዎች ሊያግዝዎት ይችላሉ። እነዚህ ቢሮዎች በስዊዘርላንድ ውስጥ እስካሁን ላልኖሩ እና እዚህ መስራት ለሚፈልጉ ሰዎች ምክር ይሰጣሉ። እውቅና ያላቸው ስደተኞች (ፈቃድ B) እና ለጊዜው ተቀባይነት ያገኙ የስደተኛ ደረጃ ያላቸው ወይም የሌላቸው (ፈቃድ F) ያላቸው ልዩ ፈቃድ አያስፈልጋቸውም። ይሁን እንጂ የእያንዳንዱ ሥራ መጀመሪያ እና መጨረሻ ጊዜ ኦፌሴላዊ ቅጽ በመጠቀም ለካንቶኑ ሪፖርት መደረግ አለበት። (የምዝገባ ሂደት፣ Meldeverfahren) ። ሪፖርት የሚደረገው በሚሰሩበት ካንቶን ነው። ምዝግባው ነጻ ነው። ጥገኝነት ጠያቂዎች (መታወቂያ N) ያላቸው ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል።

## የግል ድርጅት

የራስህ የሆነ የግል ድርጅት ስዊዘርላንድ ውስጥ ለማቋቋም፣ ያለህ ዜግነት እንዲሁም የመኖሪያ ፈቃድ ዓይነት ወሳኝ ነው። ከEU/EFTA አገሮች ለመጡ ሰዎች እና የመኖሪያ ፈቃድ C ላላቸው ሰዎች፣ የስራ ድርጅት ለመመስረት ይቀላል። የስደተኞች አስተዳደር ጽ/ቤት (Migrationsamt) ለስደተኞች የግል ድርጅት ለመመስረት መቻል እና አለመቻሉን መረጃ ይሰጣል። በካንቶን አካባቢ ለሚቋቋሙ ድርጅቶች ሎኬሽኑንን ፕሮሞሽን ለማድረግ (Standortförderung) ተግባራዊ ድጋፍ ይሰጣል።

## ጥቁር ስራ

ስራ ያለው ሰው ሆኖ የማህበራዊ የመድን ዋስትና የሌለው ፣ የስራ ፈቃድም የሌለው ወይም ገቢውን/ደሞዙን/ታክስ የማይከፍል ሰራተኛ ከሆነ፣ በሕግ መሰረት ይቀጣል። ይህም ጥቁር ስራ (Schwarzarbeit). ተብሎ ይጠራል። ጥቁር ስራ ለቀጣሪውና ለተቀጣሪው ህጋዊ እርምጃ ያስከትላል። በተጨማሪም ሰራተኞች በአደጋ ግዜ የአደጋ ጊዜ የመድን ዋስትና እና የሽምግልና እንክብካቤ የላቸውም። ተቀጣሪው ቀጣሪው በተገቢው ሁኔታ የማያሰራው ሆኖ ከተሰማው፣ ሰራተኛው ከክፍያ ነጻ የሆነ ምክር ከሕግ ምክር አገልግሎት ጽ/ቤት (Rechtsberatungsstelle) መጠየቅ ይችላል። ቀጣሪያቸው በትክክል እየቀጠራቸው እንዳልሆነ የሚያምን ማንኛውም ሰው ነፃ የህግ ምክር አገልግሎት መስጫ ማእከል (Rechtsberatungsstelle) ማነጋገር አለበት።

## ወጣቶች

በመርህ ደረጃ፣ ወጣቶች 15 ዓመት እድሜ ሲሞላቸው እንዲሰሩ ይፈቀድላቸዋል። መጠኑ ያልበዛ ቀለል ያለ ስራ /ለምሳሌ የእረፍት ግዜ ስራ/ ግን ይፈቀድላቸዋል። ወላጆች እና አሰሪዎች ወጣቶች ከአቅም በላይ ስራ እንዳይሰሩ መከታተል አለባቸው። እስከ 18 ዓመት ለሆኑ ወጣቶች ልዩ የሠራተኛ ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/arbeit/zugang-arbeitsmarkt

# ስራ ማግኘት

ከሌሎች አገሮች ጋር ሲወዳደር በስዊዘርላንድ ጥቂት ሥራ አጥዎች አሉ። ቢሆንም፣ ለስራ ፈላጊዎች የሚጠበቅባቸው መስፈርቶች ከፍተኛ ናቸው። የምስክር ወረቀቶች እና ዲፕሎማዎች በጣም አስፈላጊ ናቸው።. የጀርመንኛ እውቀት በሁሉም የሥራ ቦታ ማለት ይችላል በጣም አስፈላጊ መስፈርት ነው።

## ብቃት

በስዊዘርላንድ ውስጥ ባሉ ሁሉም ሙያዎች ውስጥ የሙያ ብቃቶች፣ ዲፕሎማዎች እና ተጨማሪ ስልጠናዎች በጣም ከፍተኛ ቦታ አላቸው ማለት ይቻላል። የውጭ አገር ዲፕሎማዎች ሁልጊዜ እውቅና አያገኙም። .ሥራ ሲፈልጉ ከቀደምት አሠሪዎችዎ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ በጣም አስፈላጊ ናቸው። ለአብዛኞቹ የስራ መደቦች የጀርመንኛ ቋንቋ እውቀት_ያስፈልጋል።

## ስራ መፈለግ

የስራ አቅርቦቶች በዕለታዊ ጋዜጦች እና በተለያዩ የኢንተርኔት ፖርታሎች ላይ ይገኛሉ። በተጎዳኝም የግል የቅጥር ኤጀንሲዎችም አሉ። መንግስታዊ ክልላዊ የሥራ ቅጥር ማዕከላት (RAV) ሥራ ሲፈልጉ ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ። ኮምፒውተሮች እና ዕለታዊ ጋዜጦች እዚያ ይገኛሉ እና የ ጽ/ቤቱ ሰራተኞ ለሥራ ፈላጊዎች የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ።

## የስራ ማመልከቻ

በአጠቃላይ ለሥራ በጽሑፍ፣ በኢሜል ወይም በኦንላይን ማመልከት ያስፈልግዎታል። ማመልከቻው ቢያንስ ሲቪ/የህይወት ታሪክ/፣ የማበረታቻ ደብዳቤ እና ከተቻለ የምስክር ወረቀቶች፣ ዲፕሎማዎች እና የስራ ድጋፍ ደብዳቤ ያካትታል። አሰሪው በማመልከቻዎ ላይ ፍላጎት ካለው፣ ለግል ቃለ መጠይቅ ይጋበዛሉ። የተለያዩ አካላት ከመተግበሪያው ጋር ነፃ ድጋፍ ይሰጣሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/arbeit/arbeit-finden

# መብት እና ግዴታ

ሰራተኞች እና አሰሪዎች የተለያዩ መብቶች እና ግዴታዎች አሏቸው። ለምሳሌ፣ ከፍተኛው የሥራ ሰዓት፣ የበዓል ቀን እና የኢንሹራንስ ሽፋን የማግኘት መብት በሕግ የተደነገገ ነው።

## የስራ ውል

አብዛኛውን ግዜ በተለምዶ የቅጥር ውሎች በጽሑፍ ስምምነት መሰረት ይፈጸማሉ። የቃል ኮንትራቶችም እንዲሁ ተፈጻሚት እና ተቀባይነትን ያገኛሉ። በስዊስ የግዴታ ህግ (Obligationenrecht) ህጋዊ ድንጋጌዎች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናሉ። አነስተኛ መሟላት ያለባቸው የሚኒሟ ደረጃዎችንም ጭምር ያካትታል።. በዚህም የተነሳ የጽሑፍ የሥራ ውል የሌላቸው ሰራኞችም ጭምር እንዲሁ የተለያዩ መብቶች እና ግዴታዎችም አላቸው።

## የተቀጣሪ ሰራተኞች መብት

በስዊዘርላንድ ውስጥ ሰራተኞች የተለያዩ ህጋዊ መብቶች አሏቸው። በጣም አስፈላጊዎቹ የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- አሰሪዎች ሰራተኞቻቸውን በማህበራዊ ኢንሹራንስ የመመዝገብ፣ የአደጋ መድን ኢንሹራንስ የማስገባት እና የተወሰነውን መዋጮ የመክፈል ግዴታ አለባቸው።
- ሁሉም ሰራተኞች ቢያንስ ለ 4 ሳምንታት የሚከፈልበት የዕረፍት ጊዜ የማግኘት መብት አላቸው። በከፊልም በሰዓት ደመወዝ ለሚከፈላቸው ሰራተኞች ወይም የከፊል ሰዓት ለሚሠሩ ሰዎች በተመጣጣኝ ሁኔታም ይሠራል።
- ከፍተኛ የሚፈቀደው የስራ ጊዜ በሳምንት 50 ሰዓት ነው። በአንዳንድ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 45 ሰዓታት ብቻ ነው።.
- ሰራተኞች በጽሁፍ የስራ ማረጋገጫ የማግኘት መብት አላቸው።
- ማንኛውም ሰው የታመመ ወይም አደጋ ቢያጋጠመው እና በድርጅቱ ውስጥ ከሶስት ወር በላይ ከሰራ፣ ለተወሰነ ጊዜ በቀጣይነት የደመወዝ ክፍያ ይከፈለዋል።
- ነፍሰ ጡር ሴቶች እና ልጅ የወለዱ ሴቶች ልዩ መብት አላቸው (የወሊድ ፈቃድ፣ Mutterschutz).
- የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ህግ (Gleichstellungsgesetz) አንድን ሰው በሥራ ላይ በጾታ ምክንያት ማዳላትን ይከለክላል።

## ደሞዝ

በBasel-Stadt ካንቶን ውስጥ በሕግ የተደነገገ አነስተኛ ደመወዝ አለ። ከጥቂቶች በስተቀር፣ ይህ በካንቶን ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ሰራተኞች ይመለከታል። በተጨማሪም፣ ብዙ ሴክተሮች ዝቅተኛ የደመወዝ ክፍያ የተደነገገው የጋራ የሥራ ስምሪት ስምምነት (Gesamtarbeitsvertrag, GAV) አላቸው።.ሴቶችና ወንዶች ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ የማግኘት መብት አላቸው። በሥራ ስምሪት ውል ውስጥ የተቀመጠው መጠን ጠቅላላ ደመወዝ ነው የሚሰራው። ሆኖም ግን፣ የሚከፈለው ገንዘብ የማህበራዊ ዋስትና ኢንሹራንስ መዋጮዎች ከተቀነሰ በኋላ የተጣራ ደመወዝ ነው (ማህበራዊ ተቀናሾች፣ Sozialabzüge). ለአብዛኛዎቹ የ B የመኖሪያ ፈቃድ ፣ የF ወይም N ፈቃድ ፣ የአጭር ጊዜ L የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የG ድንበር ተሻጋሪ ፈቃድ ያላቸው የተቀናሽ ግብሮች (Quellensteuer) እንዲሁም በቀጥታ ይቀነሳሉ። የግዴታ የጤና መድህን ኢንሹራንስ መጠን መዋጮ ክፍያ በስዊዘርላንድ ውስጥ የደመወዝ ተቀናሾች አካል አይደሉም።

## የስራ ውል መቋረጥ

የስራ ውል መቋረጥን በሚመለከት ቀጣሪዎች እና ሰራተኞች በውሉ ውስጥ የተመለከቱትን የስራ ማብቂያ የግዜ ገደብ ማክበር አለባቸው። የጊዚ ገደቡ ሳይጠብቁና አስቀንመው ሳያሳውቁ በድንገት ስራ ማቋረጥ የሚፈቀው ልዩ በሆኑ ጉዳዮች ብቻ ነው። ይህ በሚከሰትበት ሁል ጊዜ የጽሁፍ ማረጋገጫ ከነ ማቋረጫ ምክንያቱ መጠየቅ ይቻላል። የታመመ፣ አደጋ የደረሰበት፣ ነብሰ ጡር የሆነ ወይም ልጅ የወለደ ማንኛውም ሰው ከስራ ያለመባረር ልዩ ጥበቃ አለው። አላግባብ ስራን ማቋረጥ/መባረር/ በሚመለከት በፍርድ ቤት መቃወም ይቻላል። ሰራተኛው እራሱ ስራ ከለቀቀ፣ ይህ ከስራ አጥነት ኢንሹራንስ የሚሰጠውን የድጋፍ መጠን ላይ ተጽዕኖ ሊያደርግ ይችላል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/arbeit/rechte-und-pflichten

# ስራ አጥነት

ሁሉም ሰራተኞች የስራ አጥነት ዋስትና ኢንሹራንስ አላቸው። አብዛኛውን ጊዜ ሥራ አጥ የሆኑ ሰዎች ለተወሰነ ጊዜ የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ። ሥራ የሌላቸው ሰዎች በክልል የቅጥር ማእከል (RAV) መመዝገብ አለባቸው።. ይህም ሥራ በመፈለግ ያግዛቸዋል።

## የስራ አጥነት ኢንሹራንስ

የስራ አጥነት መድን ኢንሹራንስ (ALV) የመንግስት ተቋም ሲሆን ለሁሉም ሰራተኞች ግዴታ ነው። ወርሃዊ መዋጮዎች በቀጥታ ከደመወዙ ይቀነሳሉ፣ አሠሪው ግማሹን ይከፍላል። የግል ሥራ የሚሰሩ ለሥራ አጥነት መድን ዋስትና መግባት አይችሉም። ሥራ አጥ የሆነ ማንኛውም ሰው ከሥራ አጥ ፈንድ ወርሃዊ የደመወዝ ምትክ /ድጎማ/ (Arbeitslosengeld) ይቀበላል። የሥራ አጥ ክፍያ (የሥራ አጥነት ድጎማ) መቼ እና በምን መጠን እንደሚከፈል በተለያዩ ሁኔታዎች ይወሰናል። ለምሳሌ ለምን ያህል ጊዜ እንደሰራህ ወይም ስራ አጥ የተሆነበት ምክንያቱ ይወስናል።

## በስራ አጥነት ግዜ የሚወሰዱ እርምጃዎች

በመርህ ደረጃ ከመጨረሻ ከተሰራበት የሥራ ቀን በፊት በፊት፣ ቢዘገይ ሥራ አጥነት ከተሆነበት በመጀመሪያው ቀን፣ በሚመለከተው የክልሉ የቅጥር ማእከል (Regionales Arbeitsvermittlungszentrum፣ RAV) ስራ አጥነትን በሚመክት መመዝገብ ግዴታ ነው። ሁሉም ተጨማሪ ሂደቶች እዚያ ይገለጽሎታል።

## ክልላዊ የስራ ቅጥር ማዕከል

ክልላዊ የስራ ቅጥር ማእከል (RAV) ሌላ ሥራ በፍጥነት እንዲያገኙ ይረዳዎታል። የሥራ አጥነት ጥቅማጥቅም የመቀበሉ ከሆነ፣ በRAV ውስጥ ያሉት የምክር ቃለ መጠይቆች ግዴታ ናቸው። በተጨማሪም RAV ኮርሶችን ወይም የቅጥር ፕሮግራሞችን ይሰጣል። ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ ደግሞ አስገዳጅ ናቸው። በስዊዘርላንድ ውስጥ ሰርተው የማያውቁ እና ሥራ የሚፈልጉ ሰዎች እንኳን RAV መመዝገብ ይችላሉ። ቢሆንም ግን ምንም የገንዘብ ክፍያ አያገኙም።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/arbeit/arbeitslosigkeit

# የዲፕሎማ ዕውቅና

የውጭ አገር ዲፕሎማዎች እና ዲግሪዎች በስዊዘርላንድ ውስጥ ሁልጊዜ ተቀባይነት አያገኙም። እንደየሁኔታው ግን ዲፕሎማውን እውቅና ማግኘት ይቻላል። ይህ ለአንዳንድ የሙያዎ ዘርፎች ግን ግዴታ ነው።

## ዕውቅና

የውጭ አገር ዲፕሎማ ያላቸው ሰዎች በተወሰኑ ሁኔታዎች በስዊዘርላንድ ውስጥ እውቅና ሊያገኙ ይችላሉ። እውቅናው የውጭ አገር ዲፕሎማው ወይም ዲግሪው ከስዊዘርላንድ ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ ጋር እኩል መሆኑን ያረጋግጣል።.ቁጥጥር የሚደረግባቸው ሙያዎች (ለምሳሌ የነርሲንግ ባለሙያዎች፣ መምህራን፣ ወዘተ) ከሆነ በሙያውን ለመስራት የግድ ዕውቅና ያስፈልጋል። ለዕውቅናው እንደ ሙያው ወይም እንደ ትምህርቱ ዓይነት የተለያዩ አካላት እውቅና ይሰጣሉ።ለእውቅናውም ክፍያ ይከፈላል።. የብሔራዊ የዲፕሎማና የዲግሪ ዕውቅና ማዕከል (Nationale Kontaktstelle für Diplomanerkennung) ወይም ከሙያ፣ ጥናትና የሥራ አማካሪ አገልግሎት (Berufs-, Studien- und Laufbahnberatung) መረጃ ማግኘት ይቻላል።

## ደረጃ ማረጋገጥ

ቁጥጥር የማይደረግባቸው ሙያዎች ጋር በተያያዘ በስዊዘርላንድ ውስጥ ለመስራት የዲፕሎማ ወይም የብቃት ማረጋገጫ እውቅና አያስፈልግም። ለእነዚህ ሙያዎች የደረጃ ማረጋገጫ (Niveaubestätigung) ማመልከት ይችላል። ይህ የሚያሳየው የውጭ አገር ዲፕሎማ የስዊዘርላንድ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ያለውን ዋጋና ግምት ነው። ማረጋገጫው ሥራ ሲፈልጉ ሊረዳ ይችላል። ደረጃውን ስለማረጋገጥ መረጃ ከብሔራዊ የመገናኛ ነጥብ ለዲፕሎማ ዕውቅና ወይም ከስራ፣ ከጥናት እና ከሙያ ምክር አገልግሎት አገልግሎት ጽ/ቤት (Berufs-, Studien- und Laufbahnberatung) ማግኘት ይቻላል።

## የሙያ ብቃትን በኋላ ማሟላት

ሙያዊ ልምድ ያላቸው ነገር ግን እውቅና ያለው ዲፕሎማ ወይም እውቅና ያለው ብቃት ማረጋገጫ የሌላቸውና ያልተመረቁ አዋቂዎች የስዊስ መመዘኛዎችን የሚያሟላ መሰረታዊ የሙያ ስልጠና ወይም ከፍተኛ የሙያ ስልጠና ማድረግ ይችላሉ። የአሰራር ሂደቱ በቀድሞው ትምህርታቸው፣ በሙያዊ ልምዳቸው እና በእድሜያቸው ላይ የተመሰረተ ነው። ያም ሆነ ይህ፣ በቂ የጀርመንኛ እውቀት መኖር ዋና መስፈርት ነው (ደረጃ B1/B2 በGER መሠረት)። ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ከሙያ፣ ጥናት እና የስራ አማካሪ አገልግሎት ጽ/ቤት (Berufs-, Studien- und Laufbahnberatung) በነጻ መረጃ እና ምክር ማግኘት ይችላሉ። የሙያ ብቃትን ተምሮ ያሟላ ማንኛውም ሰው በስራ ገበያው ላይ ያለውን እድል ያሻሽላል እና ተጨማሪ ስልጠና የማግኘት እድልም ይኖረዋል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/arbeit/diplomanerkennung